# ማህበረ ቅዱሳን "አክራሪዎች" ወይስ ህግ አክባሪዎች?

*በታምሩ ገዳ*

አቶ መለስ ዜናዊ በቀርቡ ዙሪያ ገባውን በደጋፊዎቻቸው ከተሞላው ፓርላማቸው ፊት ቀርበው አገሪቱ ውስጥ "ተከስቷል" ወይም "እየተከሰተ ነው" ስላሉት የአክራሬነት እንቅስቃሴ ዙሪያ ትንታኔ መስጠታቸው ይታወሳል፡፡በዚህ ማብራሪያቸው ላይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የሰ/ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ስር የነበረው እና በቅርቡ በጠቅላይ ቤተክህነት ስራ አስኪያጅ ስር የሆነው እና በአገር ወስጥ ሆነ በውጪ አገር በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ጠንካራ ደጋፊዎች አንዳሉት የሚነገርለትን የማህበረ ቅዱሳን ስምን "በንጽጽርነት " ጠቅሰዋል፡፡ ይህ አገላለጻቸው በበርካታ ምእመናን ዘንድ ሰሞኑን ከፍተኛ ቅሬታን እና ሃዘኔታን የጫረ ሲሆን አንዳንድ ወገኖች ደግሞ "ሊበሏት ያሰቧትን አሞራ.... "ብለውታል፡፡ ለመሆኑ ማህበረ ቅዱሳን እንማን ናቸው ? የየትኛው የፖለቲካ ቡድን ድጋፊዎች ወይም ነቃፊዎች ናቸው ? ማህበረ ቅዱሳን ከሙስና ምን ያህል የጸዳ ነው ? አውዛጋቢው የአቡነ ጳውሎስ ሃውልት እስከአሁን ድረስ ባለመፍረሱ ተጠያቂው ማን ነው? ቤተከረስቲያኒቱ የምእመናን እና የገንዘብ ደሃ ሳትሆን በአሁኑ ወቅት በርካታ የገጠር ቤተክርስቲያናት እና ገዳማት ለምን ይፈርሳሉ? የሚሉትን እና በርካታ መሰል ጥያቄዎችን ጨምሮ ይህ ጸሃፊ ለማህበሩ አባል እና የወንጌል መምህር ለሆኑት ለዲያቆን ብርሃኑ አድማስ ነጻ እና የግል አስተያየታቸውን አንዲሰጡት ቀደም ሲል ጥያቄ እቅርቦላቸው ነበር ፡፡ የቃለምልልሱ ወቅታዊነቱን እና ጠቃሜነቱን ከግንዛቤ ውስጥ በማካተት ጸሃፊው ለአምባቢያን እንደሚከተለው አቅርቦታል ፡፡ መልካም ንባብ ይሁንሎት ፡፡

ጥያቄ፡- ማህብረ ቅዱሳን በአሁኑ ወቅት ምን አይነት መንፈሳዊ እንቅስቃሴዎችን እንደሚያከናውን በአጭሩ ቢገልጹልኝ?

ዲያቆን ብርሃኑ ፡-"በመጀመሬያ ደረጃ የማህበረ ቅዱሳን ዋንኛ አላማው በተክርስቲያኒቱን በ 21ኛው ክፍለ ዘመን ዘልቃ እንድትሽጋገር ማድርግ ነው፡፡ማህበሩ ቤተክረስቲያኒቱን እና ሃይማኖታችንን በመጠብቅ ዙሪያ ያለምንም ደርድር ፡ ያለምንም ይሉኝታ ሃይማኖታዊ ዶግማዎችን በመጠብቅ ይሰራል ፡ሰርቷልም ፡ወደፊትም ቢሆን ይሰራል፡፡በነገራችን ላይ ይህንን የምንሰራው እኛ ብቻችንን አይደለም የማህበሩን አላማን እና ተግባሩን የተገነዘቡ ወገኖቻችንን ከጎናችን በማድርግ ነው፡፡አሁን ደግሞ በጥናት የተደገፈ በአገር ውስጥ እና በውጪ አገር የሚገኙ ምእመናንን በማደራጀት ፡ ስልጠናዎችን በመስጠት በእየሃገረ ስብከቱ ለሚገኙ ካህናት እና ምእመናን ቤተክርስቲያናቸውን እንዲጠብቁ በማድረግ ይሰራል፡፡በተለይ ደግሞ አዲሱ ትውልድ ስለ ቤተክርስቲያኒቱ በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው የሚያስችለው ስልታዊ እቅዶችን ይስራል፡፡አሁንም የአራት አመት ስልታዊ እቅዶችን ጨርሷል፡፡ከዚህ በሁዋላ የረጅም አመት ፤የ አምስት አመት ወይም የአስር አመት፧እቅዶች ይኖረዋል፡፡አንዳንዶቹ እቅዶቹ ቀደም ብለው ወጥትው በተግባር ላይ የተገባባት ነገር አለ፡፡ ለምሳሌ ያህል የአብነት ፤የቆሎ፧ ትምህርት ቤቶች፡ገዳማትን በተመለከተ የአምስት አመት እቅድ ተግባሩ ተጀምሯል፡፡በዚህ በአምስት አመት ውስጥ መጀመሪያ የአብነት ፤የቆሎ፧ትምህርት ቤቶችን፡ገዳማትን በተመለከተ እንዳይጠፉ እና እንዳይዘጉ ማድረግ ነው፡፡ሁለተኛው እነዚሁ ትምህርት ቤቶች ይዞታቸውን ሳይቀይሩ እንዳሉ ሆነው አዲሱ ትውልድን ሊረዳ የሚችል ተከታታይ ስልጠናዎችን እንሰጣለን፡መምህራኑን ከረሃብ እና ከእርዛት መታደግ የቆሎ ተማሪዎቹንም ቢሆን ከቀያቸው እንዳይሰደዱ ማህበሩ የተቻለውን ሁሉ ጥረት ያደርጋል፡፡ከዚህ በሁዋላ ወደ ሌላ አምስት አመት ሲሸጋገር ደግሞ የሽሽግግር (ትራንስፎርሜሽን) ሄደት ማደረግ ነው፡፡ማህብራችን ይህንን እና መሰል ብዙ ስራዎችን እየሰራ ነው፡፡"

ጥያቄ፡- በ መንፈሳዊ አባቶች ዘንድስ ተሰሚነታችሁ ምን ያህል ነው? ልጅ ይሮጣል እንጂ አባቱን አይቀድምም ይባላል::

ዲያቆን ብርሃኑ፡-"ይሄ እውነት ነው፡፡መሰረታዊ ጥያቄም ነው፡፡በመጀመሪያ ደረጃ ማህበሩ ቤተክርስቲያኒቱን ትጠበቅ ሲል ከእነ ስርአቷ ከእነ አስተዳደር ተዋረዷ ነው፡፡ማህበሩ አባቶች ተስሚነት እንዲኖራቸው ፡ አባቶች እንዲከበሩ ፡አባቶች ውሳኔዎቻቸው ተቀባይነት እንዲኖረው ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል ፡፡ውሳኔያቸውንም ይጠብቃል፡ይቅበላልም፡፡በእነርሱ ዘንድ ያልውን ተሰሚነት በተመለከት እኛ የምንለካው ለምንሰራቸው ሰራዎች በሚሰጡት ትብብር እና በእየሃገረ ስብከቱ በሚሰጡት አገልግሎቶች ነው፡፡ እስከምናውቅው ድርስ በአገር ውስጥ ባሉ ሃገረ ስብከቶች ውስጥ በሙሉ ሰፊ ስራዎችን እንሰራለን፡፡ ይህንን የሚያመቻቹት ደግሞ ሃገረ ስብከቶቹ ናቸው፡፡አናዳንዶቹም እንዲያውውም ዘገያችሁ እያሉ እየወቀሱን ናቸው፡፡ ከዚህ አኳያ ስንለካው ከፍተኛ የሆነ ፍላጎት አለ፡፡ምክንያቱም የምንረዳቸው መምህራኑን፡ገዳማትን፡አደባራትን በመሆኑ እና ስልጠናዎችንም የምንስጥባቸው ለእነዚሁ ወገኖች ስለሆነ ነው፡፡እነርሱ የትኛው ጉዳይ እንደሚቀድም ያውቃሉ፡፡አሁን ለምሳሌ ያህል በመጨዌው የአስር አመት የስብከተ ወንጌል እራሱን የቻለ አንድ ትልቅ እቅድ አለ፡፡ይሄም እቅድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ምእመናን ቁጥር በጣም እያሽቆለቆለ ነው የመጣው፡፡አሁን ባለፈው የህዝብ ቆጠራ ላይ ስሰማው ቁጥሩ በጣም ዝቅ ብሷል፡፡"

ጥያቄ፡-ይሄ የተፈጠርው ችግር ለምንድን ነው?

ዲያቆን ብርሃኑ ፡- "ይህ ችግር የብዙ ነገሮች ድምር ነው፡፡አሁን ብንገልጻቸው የማንጨርስው በርካታ ነገሮች አሉ፡፡ አሁን ይሄንን ተቋቁመን ቢያንስ ከዚህ ቁጥር ከፍ ማድረግ ካልተቻለ ግን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ታከታዮች ቁጥር ከዚህ መቀነስ የለበትም፡፡ይሄንን ለማድረግ በደቡብ፡በምስራቅ፡፡በምእራብ ኢትዮጵያ የተጎዱ በርካታ የሃገር ስብከቶች አሉን፡፡ከእነዚህ ሃገረስብከቶች መካከል ወደ 22 ሃገረ ስብከቶች ተጠንተው በ አስር አመት ውስጥ ከ35ሚሊዮን ብር በላይ በማውጣት ቢቻል የተወሰዱትን ምእመናን መመለስ ካልሆነ የተቀሩት እንዳይሄዱ በማድረግ የሃገረ ስብከቶቹን የወረዳ ስብከቶችን በማደራጀት በገንዘብ እና በማቴሪያል ጭምር ከመርዳት ጨምሮ ስብከተ ወንጌልን በማስፋፋት ረገድ ማህበራችን ሰፊ እቅድ አለው፡፡ይህንን ሁሉን ስታይው ከእነዚህ ሃገር ስብከቶች ጋር ተፈራርሞ ጨርሷል፡፡ለምስሌ ያህል በጋምቤላ ክልላዊ መንግስት ውስጥ ባለፈው አመት የክልሉ ፕሬዜዳንትን ጨምሮ ከአምስት መቶ በላይ ምእመናን ተጠመቁ ሲባል ያንን ፕሮጅክት ስንጅምረው ከሰባት እስከ ስምንት አመታት ፈጅቶብናል፡፡ስራውን ስንጀምር ግን አንድ ሁለት እያልን አያስተማርን እና በፍላጎታቸው አየጠመቅን ነው፡፡ ወደ አምስት መቶ የሚጠጉ ምእመናኖችን ለመጥመቅ በጊዜው ልብስ እና የማህተም ክር እንኳን ለማግኘት እንቸገር ነበር፡፡ይህ እንግዴህ የሚያሳየው እያንዳንዱ ስራን ለመተግበር ምን ያህል ውጣ ውረድ አናድለው ነው፡፡ተመላላሽ ስልጠና ከሰጠናቸው በሁዋላ አስከ መንፈሳዊ ኮሌጅ የዘለቀ እውቅት የቀሰሙ በርካታ ምእመናኖችን ለማፈራት ተችሏል፡፡ያ ሁሉ ችግር እልፎ እዚህ ደረጃ ላይ ሆነን ስናየው በጣም እንደሰታለን፡፡ነገር ግን ይህ የአላማችን መጨረሻ አይደልም፡፡ገና በዙ መስራት የጠብቅብናል፡፡"



ዲያቆን ብርሃኑ አድማስ

ጥያቄ፡-ተጠያቂነትን በተመለከተ ማህብራችሁ በአገር ውስጥ ሆነ በውጭ ካሉት አባላቱ ለልማት የሚውል ገንዘብ ያገኛል፡፡ የተሰበሰበውን ገንዘብ በተገቢው ስራ ላይ ለመዋሉ እና አለመዋሉን እንዴት ማረጋገጥ ይቻላል?

ዲያቆን ብርሃኑ፡-"እዎ በብዙ መንገድ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡እውነት ለመናገር ማህበሩ በዚህ አሰራሩ ላይ በጣም የተደራጀ ነው፡፡ ግልጽነትን በተመለከተ ያለማጋነን ከብዙ ተቋሚት የተሻለ ቢሆን እንጂ የሚያንስ አይደለም፡፡ የኦዴት ሪፖርታችንን በተመለከት በእየ ስድስት ወሩ ለጠቅላይ ቤተክህነት እናቀረባለን፡፡ ከዚህ በላይ ገቤ እና ወጭያችንን በውጭ ኦዴተሮች፡ እንስመረምራልን፡፡ ከዚህ ውጭ ግን ስርአቱን ጠብቆ የመጣ ማንኛውም ሰው ሊከታተለው የሚችለው እና ሊቆጣጠረው በሚያስችለው መንገድ በራችን ዘወትር ክፍት ነው፡፡ፕሮጀክቶቻችን በተመለከት የምንሰራቸው ስራዎች ምስክሮች ሲሆኑ እንዳንድ ወገኖች በግምባር ሄድው በመመልከት የራሳቸውን እማኝነት የሚሰጡን አሉ፡፡ለፕሮጀክቶቻችን እገዛ ለሚያደርጉ ወገኖች በሙሉ የሄሳብ ሪፖርቱ በቀጥታ ይድርሳቸዋል፡፡ማህበሩ ግልጽነትን እና ተጠያቂነትን ባይከትል ኖሮ እነዚህን ዘረፈ ብዙ ፕሮጀክቶችን ስንነድፍ ደጋፊዎቻችን እንድ ሳንቲም ባልስጡን ነበር፡፡"

ጥያቄ፡- አደረጃጀታችሁን በተመለከተ አንዳንድ ወገኖች አሁን በስልጣን ላለው የኢህአዴግ መንግስት ያደራችሁ አድርገው የወስዱዋችሁዋል፡፡ ሌሎች ደግሞ ወደፊት በኢትዮጵያ ውስጥ ስር ነቀል ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ ሃይሎች የተካተቱበት ተቋም እድርገው ይፈርጁዋችሁዋል፡፡እነዚህን አባባሎች እርሶ እንዴት ያዩዋቸዋል?

ዲያቆን ብርሃኑ፡-"ሁለቱንም በወሬ ደረጃ እንሰማቸዋለን ፡፡ለአገልግሎት ወደ ውጪ አገር ሰንመጣ እንዳንድ ወገኖች ከገዢው መንግስት ጋር አገናኝተው የመናገር ነገር አለ፡፡ወደ አገር ቤት ስንመለስ ደግሞ በውጪ ካሉ ተቋዋሚዎች ጋር አገናኝተው የማየት ነገር አለ፡፡እውነት ለመናገር ይሄ አይነቱ አመለካከት ደግሞ በእኛ ዘመን አልተጀመረም፡፡ አንዳንዴ የምትሰራው ስራ የትኛውንም ጎራ እልድግፍ ሲል ያልደገፍከው አካል ሁልጊዜ የዚያኛው አካል ደጋፊ አድርጎ የመቁጠር ጠባይ አለ፡፡እንኳን በእኛ ዘመን ቀርቶ ንጉሱ ቀዳማዊ ሃይለሰላሴ በዚህ የታማሉ፡፡እንዲያውም አንድ ታላቅ የሃይማኖት አባት በአቋሚቸው የተነሳ ህይውታችውን እጥትዋል ተብሎ ይታማል፡፡"

ጥያቄ፡-እንዴት ማለት?

ዲያቆን ብርሃኑ፡- "ነገሩ እንዲህ ነው፡ እንድ ታዋቂ የቤተክርስቲያን ሊቅ የመጿጉ እለት ፤በሁዳዴ ጾም ወቅት፡፡ ለሰላሳ ስምንት አመታት በአልጋ ቁራኛ ስለ ነበረው ሰው ሲሰብኩ "ነሳ አራተከ ተንስህ ወሁር" ትርጉዋሜውም (ተነስተህ አልጋህን ተሸከመህ ሄድ) ብሎ ጌታ አዘዘው ማለት ሲሆን እኛ ሊቃውንት ይህንን ሲስብኩ ጊዜውም በኢትዮጵያ ውስጥ የተማሪዎች እንቅስቃሴ (ለውጥ) የጎላበት ወቅት ስለነበር ንጉሱ "ይህ ምስጢር እኔን ለመንካት ነው" ብለው ተረጎሙት ፡፡ የእኛ ታላቅ ሰባኬ ህይወትም በዚያ ምክንያት እንደተጠናቀቀ በስፋት ይነገራል ፡፡ እውነት ለመናገር የእኛ ነገስታት ብቻ አይደሉም፡፡ሌሎቹም ብዙ አጥፍተዋል፡፡ የእግዚአብሄር ቃል ደግሞ የት ላይ እንደሚያርፍ አታውቅም፡፡ የእግዜአብሄር ቃል በሁለት ጎን የተሳለ ሰይፍ ነው የሚባለው ለዚህ ነው፡፡ማንኛውንም የመንካት ሃይል አለው፡፡ይህማ ካልሆነ የእግዚአብሄር ቃል አትለውም፡፡በዚህ ዘመን እኛን አትደግፉንም በማለት በጠላትነት የማየት ጠባይ አለ፡፡ይሄ ደግሞ በእኛ አልተጀመረም፡በእኛም አይፈጸምም፡፡ስለዚህ ለእንደዚህ መሰሎቹ እንግዶች አይደለንም፡ተደናቂዎችም አይደለንም፡፡አንፈራቸውም፡፡አንወዳቸውም፡አንጠላቸውም፡፡የማህበሩ መሰረተ እምነት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ከሌሎች ሃይሎች ተጽእኖ ተላቀቅ ስንል የትኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ለምሳሌ የፖለቲካ ፓርቲ አባላቱን የሚመለምለው ከየተኛውም የሃይማኖት ድርጅት ነው፡፡ምናልባት በዚህ በምእራቡ አለም እንዳሉት እንዳንድ ፓርቲዎች አባላቱን የሚመለምሉት ሃይማኖትን መሰርት አደርገው ሊሆን ይችላል ፤እንደ ክርስቲያን ዴሞክራት ፓርቲዎች ፡፡ አንደዚያ ካልሆነ ድረስ ከየትኛውም ሃይማኖት በተለይ ሌብራል፤ለዘብተኛ ፡፡ በሆነ የፖለቲካ አሰተሳሰብ ውስጥ ሃይማኖት ምንም ወሳኝነት አይኖረውም ፡፡በ ቤተክርስቲያን ውስጥ ደግሞ ወሳኙ እምነት ነው፡፡የየትኛውም የፖለቲካ ርእዮት አለም አራማጅ ሊሆን ይችላል፡፡ስለዚህ ማህበረ ቅዱሳን ወደ ማህበሩ ሆነ ወድ ቤተክርስቲያን የሚመጡ ወገኖችን በፖለቲካ አስተሳሰባቸው ምክንያት እንዲገለሉ አያደርግም፡፡ ምክንያቱም ጌታም ስላላገለላቸው ነው፡፡ ጌታ እየሱስ ክርስቶስ እኮ ወደ እኔ የሚመጣውን ሁሉ አላስወጣውም ነው ያለው ፡፡ወደ ቤተክርስቲያን የሚመጣ ማንኛውም ሰው መገፋት የለበትም፡፡በእኛ አገር የአንዳንድ ወገኖቻችን የግንዛቤ ችግር መሆኑ የሚታወቀው ሩሲያዎች በፖለቲካ አመለካከታቸው ምክንያት ቤተክርስቲያናቸውን ላይ ሲለያዩ ቤተክርስቲያናቸውን የዚህ ፓርቲ ደጋፊ ወይም የዚህ ፓርቲ ተቃዋሚ ናት ሲሉ በፍጹም አትሰማም፡፡ሌላው ቀርቶ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የሌላ ሃይማኖት ተከታዮች ቢሆኑም በፖለቲካ አመለካከታቸው ቢለያዩም በሃይማኖት ረገድ ግን አንድ ናቸው፡፡እኛ ጋር ግን ብዙዎች በፖለቲካ አመለካከታቸው ምክንያት የራሳቸውን ቤተክርስቲያንን ሲበድሉ ይታያል፡፡በአገር ውስጥ ይሁን በውጬ አገር የምንገኝ ወገኖች በዚህ ጉዳይ መቼም ቢሆን ተወቋሾች ነን፡፡ከዚህ ወቀሳ የሚያመልጥ ማንም የለም፡፡"

ጥያቄ፡- ታዲያ ማህብረ ቅዱሳን በዚህ ጉዳይ አመለካከቱ ምንድን ነው?

ዲያቆን ብርሃኑ፡-"ምእመናን ወደ ቤተክርስቲያን ሲገቡ ጫማቸውን እንደሚያወልቁት ሁሉ የፖለቲካ ፓርቲ ርእዮት አለም አራማጆችም በሙሉ ወደ ቤተክርስቲያን መምጣት ይችላሉ፡፡ነገር ግን የፖለቲካ አመለካከታቸውን ግን እንደ ጫማቸው ሁሉ እደጃፍ ላይ አውልቅው ወደ ቤታቸው ሲሄዱ ያድርጉት ነው መልእክታችን ፡፡በዚህ አቋም መጣላት የለባቸውም፡፡ማህበረ ቅዱሳንም የቆመለት አላማ ይሄው ነው፡፡አባላቱ ግን ቀደም ሲል አንደነገርኩህ ከየትኛውም አስተሳሰብ አራማጆች ሊመጡ የችላሉ፡፡ ማንኛውም አባላችን የትኛው የፖለቲካ አመለካከት አንዳለው አናውቅም ፡፡ ይሄ አላማችንም ፡ መብታችንም አይደለም፡፡ማወቅም አንፈልግም፡፡"

ጥያቄ፡- እንደሚታወቀው በአገር ውስጥ ያለው ቅዱስ ሲኖዶስ ከወራት በፊት በርካታ ውሳኔዎችን ማስተላለፉ ይታወቃል፡፡ ለምሳሌ ያህል አወዛጋቢው የአቡነ ጳውሎስ ሃውልት አንዲፈርስ መወሰኑን አስታውሳለሁ፡፡ ታዲያ ይሄ ውሳኔ ከምን ላይ ደረሰ?

ዲያቆን ብርሃኑ፡-"እንግዲህ ሃውልቱ ልክ እንደ እግር ኳስ ሁሉም ሰው የሚያየው ነገር ስለ ሆነ ትልቁ ጥያቄ እርሱ ይሁናል እንጂ ቅዱስ ሲኖዶሱ ውሳኔ አስተላልፎባቸው ነገር ግን ያልተፈጸሙ ብዙ ውሳኔዎች አሉ፡፡ይህንን ነጠሎ ከማየት ሁሉኑም በጥቅሉ ማየት ይቻላል፡፡ ከዚያ ይልቅ ቢፈጸሙ የሚጠቅሙ ብዙ ውሳኔዎች ቅርተው ይሆናል፡፡"

ጥያቄ፡- ለምሳሌ ያህል ቢጠቅሱልኝ...?

ዲያቆን ብርሃኑ፡-"ሁሉንም ብዘረዝራቸው ለአምባቢያን ብዙ የማይጠቅሙ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡አንዱን እንኳን ለምሳሌ ያህል ብጠቅስልህ ቤተክርስቲያኒቱን ወደ 21ኛው ክፍለ ዘመን ማሸጋገር የሚለው እቅድ እኮ ትልቅ ስራ ነው፡፡ያንን እቅድ ብናሳካው ኖሮ አሁን ያነሳሃቸው ነገሮች ሁሉ አወዛጋቢ ግዳዮቻችን አይሆኑም ነበር፡፡"

ጥያቄ ፡- ታዲያ አብዛኞቹ ውሳኔዎች ተፈጻሚ አልሆኑም ካሉኝ ድክመቱ የማን ነው? የቅዱስ ሲኖዱሱ ነው ማለት አይቻልም?

ዲያቆን ብርሃኑ ፡-"እርሱ ላይ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ ነገር ግን የሲኖድሱ ብቻ ስህትት ነው እንለውም፡፡ወደ አፈጻጸም ስንመጣ ቅዱስ ሲኖዶሱ ትልቁ የውሳኔ አካል እና የማስፈጸም አቅም እና ሃላፊነቱ ስላለው ትልቁን ሃላፊነትን ሊወስድ ይችላል፡፡ ነገር ግን አጠቃላይ ቤተክርስቲያኒቱን ወደ ዘመናዊ የአስተዳደር ስርአት ለመለወጥ እስካልተቻለ ድረስ እንደው አሁን ባለው አካሄድ ብቻ ከተጓዝን ውሃ ቢወቅጡት አይነት ነው የሚሆነው ፡፡አሁን የመጣንበት የአስተዳደር ስርአት ወደ ሃምሳ አመት ሊሆነው ነው፡፡ እንግዲህ በሃምሳ አመታት ውስጥ ያልተቀየረ ብቸኛው የአስተዳደር ስርአት ሊሆን ይችል ይሆናል፡፡አሁንም ሊቀይሩ የማይገባቸው በርካታ ነገሮች ሊኖሩት ይችላሉ፡፡ነገር ግን መቀየር ያለባቸው ብዙ ሁኔታቸው አሉ፡፡መሰረታዊ የሆኑ ነገሮች ካልተለውጡ እንዲያው ሄደህ ትንሿ ነገር ላይ የማተኮር ጉዳይ ሊያሰኝ ይችላል፡፡ዝናብ እስካለ ድረስ ጎርፍ መኖሩ እንደማይቀር ሁሉ ዘመናዊ አስተዳደር ቢመሰረት ኖሮ አሁን የምንከራከርባቸው ሃሳቦች ባልተከሰቱ ነበር፡፡ በነገራችን ላይ ይሄ የምነግርህ ሁሉ ማንንም ወክዮ ሳይሆን የግሌ አስተሳሰብ መሆኑን ልገልጽልህ እፈልጋለሁ፡ ደከመቱን በተመለከተ የሁላችንም ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን በጠባይዋ ፖለቲካዊ ተቋም አይደለችም፡፡አብዮታዊ በሆነ ነገር ለውጥ አይመጣባትም፡፡ፖለቲካ የአመለካከት ወይም የአይዲዎሎጂ ጉዳይ ነው፡፡ ግለሰብአዊ ጉዳቱ እንዳለ ሆኖ ባይሳካልህ ብዙ አይቆጠቁጥህም፡፡ ሃይማኖት ግን አንደዚያ አይደለም፡፡ ግለሰባዊ ጉዳትህ ሁሉ ትልቅ ይሆናል፡ ትጠራጠራለህ፡ትማረራለህ፡ከእግዚአብሄር ጋራ ትጣላለህ፡፡ጉዳቱ በአጠቃላይ ትልቅ ነው፡፡እና አነዚህን ሁሉ ስታስባቸው ሃላፊነቱ ቅድም ለመጥቀስ እንደሞከርኩት ተጠያቂነቱን በተመለከት የቤተክህነቱ፡የሲኖዶሱ ፡የካህናቱ ድርሻ ከፍ ያለ ቢሆንም የሁላችንም ድርሻ አለበት፡፡እውነት ለመናገር ፍርደ ገምድል መሆን አይጠበቅብንም፡፡ቤተከርስቲያኒቱን ማፈራረስ የሚፈልግ አካል ግን አስተያየቱን በፈለገው መንገድ መስጠት ይችላል፡፡ይህ ማለት ደግሞ ስህተቱን ሁሉ ይቀበል ማለት አይደለም፡፡ ስህተቶች ሲከሰቱ አታውግዙ ማለትም አይደለም ፡፡ሲያወግዙ ግን የግድ በጩሀት አይደለም፡፡ ለሁሉም ስርአት እና መንገድ አለው፡፡ ከርስትና ማለት እኮ የሌላውን ህሌና ላለመጉዳት መጠንቀቅ ማለት ነው፡፡አድገቷን የሚፈልገው ማንኛውም አካል ግን አስተያየቱ ሁሉ በጥንቃቄ ሊያደርገው ይገባል፡፡ በዚያ መንገድ ለእይምሮ በሚመች ተሳስቷል የምትለው አካል ሊሰማህ በሚችለው መንገድ ቢሆን ጥሩ ነው፡፡ይህ ሁሉ አሁን የምናያቸው ችግሮች ለብዙ አመታት የተነከባለሉ ችግሮቻችን ውጤት ነው፡፡አሁን የሚያሳየን ጥሩ ነገር ህዝቡ መቆርቆር ጀምሯል፡ መጠየቅ ጀምሯል፡መሰተካከል አለበት ብሎ የሚያምነው ጉዳይ ዙሪያ መወያየት ጀምሯል፡፡ ይህ ሁሉ አንድ ትልቅ አውንታዊ እድገት ነው፡፡ ነገር ግን ፍላጎቱን ሊያመጣው የሚችለው ግን ክሱ እና ወቀሳው ብቻ አይደለም ፡፡ መተሳሰብም ያስፈልጋል፡፡ እውነት ለመናገር ቤተክርስቲያን የክርስቶስ ስለሆነች ይዋል ይደር አንጂ ክርስቶስም የሚያመጣው ነገር አለ፡፡ ይህ ካልሆን ግን በፍጥነት ወደ መጠላላት ፡መራራቅ፡መለያየት ከዚያም አልፎ ወደ ጠፋፋት ነው የምናመራው፡፡ቅድም ያልናቸው መለያየቶች ዝም ብለው የተፈጠሩ አይደሉም፡፡ እራሳችን ለራሳችን መፍትሄ ፈላጊዎች ካልሆንን ወደ የባሰ መለያየት ነው የምናመራው፡፡ በጣም ገለሰባዊነቶች እየነገሱ ይሄዳሉ፡፡እርሱ ደግሞ ውጤቱ ምናልባት ለሌላ ተቋም፡ለሌላ አይነት አደረጃጀት ሊጠቅም ይችል ይሆናል፡፡ በገሃዱ አለም ኩባንያዎች አየተከፋፈሉ፡እየተፎካከሩ እራሳቸውን ችለው እንዲያድጉ ቢደራጁ ሊጠቀሙ ይችሉ ይሆናል፡፡ ይሄ አካሄድ ግን ለሃይማኖት በፈጹም አይሰራም፡፡"

ጥያቄ፡- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በብዙ ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ተከታዮች አያሏት በተቃራኒው ደግሞ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የሚገኙ ብዛት ያላቸው ቤተክርስቲያንት ፡ገዳማት ፡የአብነት ትምህርት ቤቶች ሲፈራርሱ እና ሲዝጉ ይታያል...

ዲያቆን ብርሃኑ፡- "ችግሩ ልክ እንደ አገራችን ኢትዮጵያ ነው ፡፡ ኢትዮጵያ እምቅ ሃብት ያላት በተቃራኒው ግን ደሃ አገር ናት፡፡ ቤተክርስቲያኒቱም ቢሆን በአቅም ደረጃ ከየትኛውም ተቋም የተሻለች ነች ፡፡ቀደም ብዬ ለመግለጽ አንደሞከርኩት የ ዘመናዊ አሰራር፡ የአስተዳደር .ወዘተ ለውጥ አምጥትን ብንሄድ ቤተክርስቴያኒቱ ብቻ አይደለችም በስሯ ያሉ የበርካታ ወገኖቻችን ህይወት ጭምር በተቀየረ ነበር፡፡"

ጥያቄ፡- በሰተመጨርሻ ለአምባቢዎች የሚያስተላልፉት መልእክት ካሎት?

ዲያቆን ብርሃኑ ፡- "እኔ የምለው ነገር ቢኖር ቤተክርስቲያናችን የጋራችን ናት ፡የሁላችንም ሃሳብ የጠቅማታል፡ በስርአት ካልሆነ ደግሞ የሁላችንም ሃሳብ ይጎዳታል፡፡የሁላችንም ጥረት ያስፈልጋታል ፡፡ሁላችንም ወደ አንድ ቦታ መሰባሰብ አለብን፡፡ግድ የለም አስር አመት ሆነ ሃያ አመታት ሊፈጅ ቢችል እንኳን ከማንኛውም ተጽእኖ ነጻ የምትሆንበት ግብን መቀየስ አለብን፡፡በየትኛውም ወገን ያሉ የቤተክርስቲያኒቱ አባቶች ፡ አገልጋዮች ሆኑ ማእመናን እንዲሁም ለቤተክርስቲያኒቱ እናስባለን የሚሉ ወገኖች ሁሉ ግድ የለም አሁን ላንረዳዳ አንችላለን ፡ ላንግባባቸው የሚችሉ በርካታ ነጥቦች ሊኖሩ ይችላሉ፡የሚያከራክሩን የሚያጨቃጭቁን ጉዳዮች ይኖራሉ ፡፡ነገር ግን የእነዚህ ሁሉ አላማው እነዚህን ችግሮቻችንን የሚፈታ እና ወደ አንድነት የሚያመጣን መሆን አለበት፡፡ቢያንስ

በሁላችንም ዘንድ ይሄንን ግባችን ብናደርገው የፈጀው ጊዜ ፈጅቶ ወደ አንድነት መምጣታችን አይቀርም፡፡በሁዋላ ደግሞ መስዋትነቱን የሚከፍለው ትውልድ ሊመጣ ይችላል፡፡አሁን እኮ ይቅርታ የሚጠይቅ መሰዋትነት የሚከፍል ሰው ነው ያጣነው ፡፡የሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን በ17ኛው ክፍለ ዘመን በ አራት የተለያዩ ፓትሪያርኮች መመራት ጀምራ ነበር ፡፡ያንን ሁሉ ችግራቸውን ለመቅረፍ እና አሁን ወዳለቸበት የአንድ ፓትሪያርክ የአቡነ ቤኔዲክት አመራር ለመተዳደር አርባ አመታት ፈጅቶባቸዋል፡፡ግን ቤተክርስቲያናቸውን አንድ ማድረግ ችለዋል፡፡ የተለያዩ የፖለቲካ አመለካከቶች ቢኖሩንም የብዙ ቋንቋዎች ተናጋሪዎች ሃዝቦች ብንሆንም ግን አንድ አገር እና አንድ ህዝብ ነው ያለን፡፡ አሁን እኛ አንድ አገር ያለን ህዝቦች መካከል የሚገኙ የተለያዩ ፓርቲዎች ቀጥተኛም ይሁን የእጅ አዙር ተጽእኖዎች ናቸው አንደዚህ ይሚለያዩን ፡፡ነገር ግን የተለያዩ መንግስታት ፍላጎት እኮ የሮማ ካቶሊክ ቤተከርስቲያንን አላጠፏትም፡፡ስለዚህ የእኛ የሁላችንም ሃሳብ ቤተክርስቲያናችንን አንድ የማድረግ ፡ወደዚያ የመገስገስ የሚታለፉ ቸግሮችንን የማለፍ ፡የቅር የሚባሉትን ይቅር የማለት፡ይቅርታ የመጠየቅ ፍላጎቶቻችን እንዲጎለብቱ መታገል አለብን፡፡እነዚህ የሚቃወሙንን ፡የሚያሰናክሉንን አመለካከቶችን ቀስ እያልን ትክክለኛ በሆነ መንገድ መሟገት አለብን፡፡ ይሄን ማስፋፋትም አለብን፡፡ የሄን ማድረግ እስከቻልን ድረስ እግዚአብሄርም ይረዳናል ብዮ አምናለሁ፡፡"

ጥያቄ፡-ለሰጡኝ ሰፊ ማብራሪያ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

ዲያቆን ብርሃኑ፡-"እኔም እድሉ ስለተሰጠኝ እግዜአብሄር ይስጥልኝ"

ለተጨማሪ ማብራሪያ ወይም አስተያየት ጸሃፊውን በዚህ አድራሻ ማግኘት ይችላሉ፡- tamgeda@gmail.com